| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ። " |
| ርእስ ፤ | "ስለ ፡ ኦጋዴን" |
| ደራሲ ፤ | መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ (1891-1971 ፡ ዓ.ም.) ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | ከ"ትዝታዬ ፤ ስለ ፡ ራሴ ፡ የማስታውሰው ፤ 1891-1923 ፡ ዓ.ም. ። " ፡ ከገጽ ፡ 185-186 ፡ የተቀዳ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ።

History Column | colonne d'histoire

## *"ስለ ፡ ኦጋዴን ። "*

*መርስዔ ፡ ሐዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ (1891-1923 ፡ ዓ.ም.) ።*

(*"ትዝታዬ ፤ ስለ ፡ ራሴ ፡ የማስታውሰው ፤ 1891-1923 ፡ ዓ.ም. ። "* ፡ ከገጽ ፡ 185-186 ፡ የተቀዳ ። )

---

ኦጋዴን ፡ ከጅግጅጋ ፡ አውራጃ ፡ በስተደቡብ ፡ የሚገኝና ፥ የግዛቱ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ የኾነ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ነው ። የሐረር ፡ እንደራሴ ፥ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ጋሪ ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ኦጋዴን ፡ ወርደው ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ሥራን ፡ ሲያቋቁሙ ፡ መክረማቸውን ፡ ሰማን ። ይህም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

አገሩን ፡ በየወረዳው ፡ እየከፈሉ ፥ 12 ፡ ከተማዎችን ፡ አቋቋሙበት ። በየከተማዎቹም ፡ ጸጥታ ፡ ጠባቂ ፡ ወታደርና ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሹም ፡ እየመደቡ ፡ አስቀመጡባቸው ። የተቋቋሙት ፡ ከተማዎች ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ሲኾን ፥ ላንዳንዶቹ ፡ ዐዲስ ፡ ስም ፡ አወጡላቸው ። ይህም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ኤል ፡ ጉበያ ፡ (አኹን ፡ *"ጎረቤት"* ፡ ብለውታል) ፤

ፊቅ ፤

ገላልቻ ፤

ወረ ፡ ሂርሲ ፤

ደጋ ፡ ሐመዶ ፡ (አኹን ፡ *"ታመነ"* ፡ ብለውታል) ፤

በለምበል ፤

ጣናን ፤

ሳሰበኔ ፤

ቆራሄ ፡ (አኹን ፡ *"ርጎ"* ፡ ብለውታል) ፤

ቀልቀሎ ፤

ቡስሌ ፡ (አኹን ፡ *"ፋሲካ"* ፡ ብለውታል) ፤

ጀድሌ ፡ (አኹን ፡ *"መትረየስ ፡ በር"* ፡ ብለውታል) ።

ስያሜ ፡ ስለተሰጠበት ፡ ስለቃሉ ፡ ትርጓሜ ፡ የሰማኹት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። *"ጎረቤት"* ፡ መባሉ ፡ ለሐረር ፡ የሚቀርብ ፡ በመኾኑ ፤ *"ርጎ"* ፡ መባሉ ፡ አየሩ ፡ ጥሩ ፡ በመኾኑ ፤ *"ፋሲካ"* ፡ መባሉ ፡ በምቾት ፡ የሰነበቱበት ፡ በመኾኑ ፤ *"መትረየስ ፡ በር"* ፡ መባሉ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ወሰን ፡ ገፍተዋል ፡ በሚባልበት ፡ ክፍል ፡ ስለሚገኝ ፥ ክርክር ፡ ያለበት ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተነግሮኛል ።

በዚህ ፡ ዓመት ፡ የመኪና ፡ መንገዶች ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ስለ ፡ ተያዘ ፥ ከድሬዳዋ ፡ እስከ ፡ ሐረር ፡ የመኪና ፡ መንገድ ፡ ተሠርቶ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ መኪና ፡ ገብቷል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፥ ከሐረር ፡ ወደ ፡ ጂግጂጋ ፡ የመኪና ፡ መንገድ ፡ ተዠምሮ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።




---


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።